سبعين مسألة في الصيام باللغة الأمهرية (الإثيوبية)

للشيخ محمد صالح المنجد

በአማረኛ ቋንቋ ፆምን የሚመለከቱ ሰባ /70/ ጠቃሚ ነጥቦች

ሸይኽ ሙሐመድ ሳሊህ አልሙነጂድ ያዘጋጇቸዉ የሆኑ

ምስጋና ሁሉ ለአላህ የተገባ ነዉ::

እናመሰግነዋለን እገዛዉንም ምህረቱንም እንጠይቀዋለን ከነፍሶቻችን ክፋትና ከስራዎቻችን መጥፎ በአላህ እንጠበቃለን አላህ ቅኑን መንገድ የመራዉ ሊያጠመዉ የሚችል የለም አላህ ያጠመመዉ ደግሞ ትክክለኛዉን መንገድ ሊመራዉ የሚችል አካል የለም ከአላህ በስተቀር ሌላ በእዉነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩን እሱ አጋር የሌለዉ አንድ አምላክ መሆኑን እመሰክራለሁ ሙሐመድ ﷺ የአላህ አገልጋይና መልዕክተኛ መሆናቸዉን እመሰክራለሁ :: አላህ ﷻ መልካም ነገሮችን ባዘሉ ወራት ምክንያት ለባሮቹ ወደር የለሽ ፀጋን ለግሷል በነኚህ ወራት መልካም ስራዎች ምንዳቸዉ ይነባበራል ወንጀሎች ይታበሳሉ ደረጃዎች ይጨምራሉ ከነኚህ መልካም ነገሮችን ካዘሉ ወራት መካከል ትልቅ ግምት የሚሰጠዉ አላህ ﷻ በባሮቹ ላይ ግዴታ ያደረገዉ የረመዷን ወር አንዱ ነዉ እንዲሁም በጉጉት እንዲጠቀሙበት አድርጓል ግዴታ ስላደረገዉም ያመሰግኑት ዘንድ አመላክቷል ይህ የረመዷን ኢባዳ ደረጃዉ ከፍ ያለ ስለሆነ ከዚህ ወር ጋር ትስስርነት ያላቸዉን ህጎች የፆም ህጎችን ፣ስርዓቶችን እና መማር ግዴታ ይሆናል ይህ መልዕክት ሱናዎችን ጠቅለል ባለ መልኩ አቅፎ የያዘ መልዕክት ነዉ::

ፆም ማለት ምንዲን ነዉ

1. ፆም በቋንቋ ደረጃ መከልከል ማለት ሲሆን ግን እንደኢስላም ህግ ሌሊቱ ከመንጋቱ በፊት ለመፆም ኒያ(ሀሣብ) በማድረግ አላህን በማምለክ አላማ ጠዋት ሁለተኛዉ ጎህ ከቀደደበት (ከወጣበት) ጀምሮ እስከ ፀሐይ መጥለቅ ድረስ ፆምን ከሚያበላሽ ነገር መከልከል ነዉ::

የፆም ህግ(ብይን)

2. የረመዷን ወር መፆም ግዴታ ለመሆኑና ምንም ምክንያት የሌለዉ ሰዉ በረመዷን ወር ካፈጠረ በርግጥ ትልቅ ወንጀል የፈፀመ ለመሆኑ ሙስሊሞች ተስማምተዋል::

የፆም ትሩፋት

3. ከፆም ትሩፋቶች መካከል አላህ ፆምን ለራሱ መርጦ በሱ የተነባበረን ምንዳ የሚከፍል ፣ የፆመኛ ዱዓ የማይመለስ ፣ ፆመኛ ሰዉ ሁለት ደስታዎችን ማግኘቱ ፣ፆም ለባሪያ የቂያማ ቀን መሸምገሉ ፣የፆመኛ ሰዉ አፍ ጠረን አላህ ዘንድ ከሚስክ ሽታ የበለጠ መዓዛ ያለው መሆኑ ፣ፆም ከገሀነም እሳት የሚጠብቅ መከላከያ ምሽግ እና ጋሻ መሆኑ፣ ጂሃድ ላይ አንድ ቀን የፆመ በዚህ ቀን ምክንያት አላህ ፊቱን ከሳት የሰባ ዓመት ያህል የሚያርቀዉ መሆኑ ፣ በገነት ዉስጥ ከፆመኞች በስተቀር ማንም ሊገባበት የማይችል የሆነ ረይያን የሚባል በር መኖሩ ። (እነኝህ ለምሳሌ ያህል የቀረቡ የረመዷን ትሩፋቶች ናቸዉ።

* የረመዷን ፆም ከኢስላም ማዕዘናት አንዱ ነዉ። ቁርዓን የወረደበት ወር ነዉ የተላቀች ሌሊት ከአንድ ሺ ወራት የምትበልጥ የምትገኝበት ነዉ የረመዷን ወር ሲገባ የሰማይ(የጀነት) በሮች ይከፈታሉ። የገሀነም በሮች ይዘጋሉ ሰይጣኖችም በሰንሰለት ይታሰራሉ። የረመዷን ፆም እንዴ አሥር ወሮች ይቆጠራል። (ይህን ለማብራራት አንድ በጎ ስራ አላህ ዘንድ አሥር እጥፍ ምንዳ አለዉ ። የረመዷን ፆም በአስር ወሮች ይቆጠራል ፣ስድስት የሸዋል ቀናት ደግሞ በሁለት ወሮች ይቆጠራሉ ድምራቸዉ 12 ወራት (አንድ ዓመት) ይሆናል። በዚህ ዓይነት ፆሙ በየዓመቱ ከተዷጋገመ ዕድሜ ልክ እንደመፆም ይቆጠራል ማለት ነዉ። (አላህ አዕለም)

<u>የፆም ጥቅሞች(ፋዲዳዎች)</u>

4. ፆም ከተቅዋ(አላህን ከመፍራት) ጋር የተሳሰሩ ብዙ ጥቅሞችን ያዘለ ነዉ ፆም ሰይጣንን ለማሸነፍ ፣ስሜትን ለመስበር የሰዉነትን ክፍል ለመቆጣጠር መንገድ ነዉ። ከመጥፎ ስሜትና ወንጀል የመራቅ ፍላጎትን ያዳብራል እንዲሁም ከስርዓቶች ና ከቃል ኪዳን ጋር መላመድን ያስተምራል ይህ ወር የሙስሊሞች አንድነት የሚጀምርበት ወር ለመሆኑ አዋጅ ጥቆማ አለበት።

<u>የፆም ስርዓቶችና ሱናዎች</u>

5. ግዴታ ወይም ተወዳጅ የሆነ አለ እሱም፡-

*ለኩለ ሌሊት ምግብ ግምት መስጠትና ማዘግየት

* ፊጥር ማፋጠን ረሱል ﷺ እንዲህ ብለዋል፡-(ሰዎች በጎ ነገር ከመፈፀም አይወገዱም ፆማቸዉን ወቅቱ እንደገባ በአስቸኳይ እስካቆሙ (እስካፋጠሩ) ድረስ ። ረሱል ﷺ ከመስገዳቸዉ በፊት በተምር እሸት ያፈጥሩ ነበር ይህን ካላገኙ በደረቅ ተምሮች ይህን ካላገኙ በዉሃ ያፈጥሩ

ነበር:: ካፈጠሩ በኋላ ጥማቱ ሄደ ፣ጅማቶችም ራሱ፣ በአላህ ፍቃድም ምንዳዉ ፀና ይሉ ነበር::

* ተገቢ ያልሆኑ መጥፎ ነገሮችንና ወንጀሎችን መራቅ

*መልካም ነገሮች እንዲወገዱና እንዲጠፉ እነዲሁም መጥፎ እንዲስፋፋና እንዲከሰት ከሚያደርጉት ጥቂቶቹ

(ለምሳሌ) :- አፈ ታሪክ ተረቶች ፣ ሙሰልሰሎች ፣ ድራማ ፣ኳስ ጨዋታ ፣ከጥቅም ያገለለ የሆነ ስብሰባ ና መንገዶች ላይ በመዝናናት ጊዜን ማባከን ... ናቸዉ::

* ምግብ መቀነስ ረሱል ﷺ የአደም ልጅ ከዕቃዎች ሁሉ እንደ ሆድ ያለ መጥፎ ዕቃ አይሞላም ብለዋል::

* በዕዉቀት ፣ በገንዘብ ፣ በስልጣን ፣ በአካልና በጥሩ ፀባይ ቸር መሆን ረሱል ﷺ በእርግጥ በመልካም ነገር እንደሳቸዉ ቸር ማንም አልነበረም በተለይም ረመዷን ወር ላይ::

<u>በተከበረዉ ወር ዉስጥ መሰራት ያለበት ነገር</u>

* ነፍሶችን እና ሁኔታዎችን አላህን ለማምለክ ዝገጁ ማድረግ፣በፍጥነት ወደ አላህ በመመለስ ተዉባህ ማድረግ ፣ረመዷን በመግባቱ መደሰት ፣ ፆምን በሚገባ መፆም፣ ተራዊህን በፍርሀት መስገድ ፣ መካከለኞቹ አሥር ቀናት ላይ አለመሰላቸት ፣ለይለተል ቀድርን መጠባበቅ ፣ ምፅዋት(ሶደቃ) ማብዛትና(የመጨረሻ አሥር ቀናት) እዕቲካፍ መቀመጥ ..

* ለረመዷን ወር እንኳን በሰላም አደረሳችሁ ቢባል ችግር የለዉም ረሱል ﷺ ረመዷን በመግባቱ ለሶሃቦች እንኳን ደስ አላችሁ ይሉ ነበር ትኩረት እንዲሰጡትም ቅስቀሳ ያደርጉ ነበር::

<u>የፆም ህጎች</u>

6. ከፆም በተከታታይ መፆም ግዴታ የሆነ አለ (ለምሳሌ)፡-የረመዷን ፆም፣ በስህተት ሰዉ የገደለ ማበሻ(ከፍፋራ)ፆም ፣ሚስቱን እንደ እናቴ ጀርባ ነሽ ያለ የቅጣት ክፍያ (ከፍፋራ)ፆም፣ ረመዷን ዉስጥ ቀን ከሴት ጋር ግንኙነት የፈፀመ ...

እንዲሁም በተከታታይ መፆም ግዴታ ያልሆነ አለ(ለምሳሌ)፡-የረመዷን ቀደ ፣ ማረድ ያልቻለ ሐጃጅ የሚፆማቸዉ አሥር ቀናት..

7. ግዴታ ያልሆነ የፍላጎት ፆም ግዴታ የሆነን ፆም እንኸን ይጠግናል ::

8. ጁሙዓን ከቀናት ለይቶ መፆም ክልክል ነዉ እንዲሁም ቅዳሜን ግዴታ የሆነ ፆም ሲቀር ፣ እንዲሁም ዓመትን በሙሉ መፆም፣

ያለፊጥር(ፀሀይ እንደገባች ሳይመገብና ሳይጠጣ) ፆምን መቀጠል፣ሁለቱን የሚድ ቀናት እና አይያመተሸሪቅም መፆም ሀራም ነዉ።።

<u>የረመዷን ወር መግባት</u>

9. የረመዷን ወር መግባት ጨረቃን በማየት ወይም የሸዕባን ወር ሰላሳ ቀን በመሙላት ይታወቃል። ነገር ግን በካላንደር መጠቀም ቢድዓ ነዉ።።

<u>ፆም በማን ላይ ግዴታ ይሆናል</u>

10. ሙስሊም በሆነ ፣ለአቅመ አዳም በደረሰ ፣ጤናማ አዕምሮ ባለዉ፣ መንገደኛ ባልሆነ ፣ለመፆም በሚችል እና ፆምን ከሚከለክሉ ነገሮች ነፃ መሆን (ለምሳሌ)፡-ከወር አበባና ከወሊድ ደም ።።

11. ሰባት ዓመት የሆነዉ ህፃን የሚችል ከሆነ እንዲፆም ይታዘዛል። እንደዉም ከፊል ዑለማዎች አሥር ዓመት ላይ የማይፆም ከሆነ ለሶላት እንደሚገረፍ ሁሉ ለፆምም ይገረፋል ብለዋል።።

12. ግማሽ ቀን ላይ ከሃዲ(ካፊር) የነበረ ቢያምን ወይም ህፃኑ ለአቅመ አዳም ቢደርስ ወይም የአዕምሮ በሽተኛ ቢሻለዉ ሁሉም የቀረዉን ቀን መከልከል ግዴታ ይሆንባቸዋል። ግን ከወሩ ያመለጣቸዉ ቀዷ የለባቸዉም[1] ።።

13. የአዕምሮ በሽተኛ ተጠያቂ አይደለም አንዳንድ ጊዜ የሚሻለዉ ሌላ ጊዜ የሚታመም ከሆነ በሽታዉ ሲያገልለት(ሲወገድለት) መፆም ግዴታ ይሆንበታል በሚታመም ጊዜ ግን ግዴታ አይሆንበትም[2] ።። በሰይጣን ከመለከፉ የተነሳ(አዉድቅ) የጣለዉ ሰዉ ካለፈው ህግ ጋር ተመሳሳይ ነዉ[3]

14. ረመዷን ወር ዉስጥ የሞተ ሚቹም ሆነ ዘመዶቹ በቀሩት ቀናት ተጠያቂ አይደሉም።።

15. የረመዷን ፆም ግዴታ መሆኑን ያላወቀ እንዲሁም መመገብ እና ከሴት ጋር ግንኙነት መፈፀም ሀራም መሆኑን ያልተረዳ ሰዉ ይህን

---

[1] እንዲሁም ትክክለኛዉ አቋም ይህን ቀን ቀዷ ማዉጣት የለባቸዉም የሚለዉ ነዉ።። ተርጓሚው

[2] የአዕምሮ በሽተኛ መጀመሪያ ፆም ግዴታ ስላልሆነበት ቀዷ የለበትም።።ተርጓሚው

[3] ነገር ግን ዐሊሞች ይህ ሰዉ የመፆም ግዴታ ስላለበት ቀዷ ግዴታ ይሆንበታል ብለዋል ።።ተርጓሚው

ቢፈፅም ያቀረበዉ ምክንያት ተቀባይነት ያለዉ ከሆነ በርካታዎቹ ዐሊሞች ተቀባይነት አለዉ ብለዋል፡፡ ግን ሙስሊሞች መካከል የሚኖር ሆኖ መጠየቅና መማር እየቻለ ከሆነ ይህን የፈፀመዉ ያቀረበዉ ምክንያት ተቀባይነት የለዉም ::

<u>ጉዞ ላይ መፆም</u>

16. ጉዞ ላይ ማፍጠር መስፈርት አለዉ በርቀት ወይም ከሰዎች ልምድ አንፃር መንገድ መባል አለበት እንዲሁም የሚኖርበትን ሀገርና ከሀገሩ ጋር የተያያዙ አካባቢዎችን ያለፈ መሆን ፣ዐሊሞች ጉዞዉ ወንጀል የሚሰራበት እንዳይሆን ይላሉ፡፡ ተጨማሪም ጉዞዉን ምክኒያት በማድረግ ለማፍጠር ያሰበ መሆን የለበትም ::

17. መንገደኛ ማፍጠር እንደሚችል ሙስሊሞች ተስማምተዉበታል ጠንካራ ቢሆንም ደካማ ::ችግር ላይ የሚወድቅ ቢሆንም ባይሆንም

18. በረመዷን ጉዞ የወሰነ እስከሚጓዝ ድረስ ለማፍጠር ኒያ ማድረግ የለበትም ከወጣ በኋላና የሚኖርበትን ሀገር አካባቢና ቤቶች ካለፈ በኋላ ቢፆን እንጂ፡፡

19. ምድር ላይ እያለ ፀሀይ ከገባች በኋላ አፈጠረ ከዚያ አዉሮፕላኑ ጉዞ ቢቀጥልና ፀሀይ እንዳልገባች ቢረዳ በፆሙ ላይ መቀጠል ግዴታ አይሆንበትም ለምን ቢባል(ምድር ላይ እያለ) ፆሙን በሙሉ ስላጠናቀቀ

20. እሚጓዝበት ሀገር ከደረሰ በኋላ ከአራት ቀናት በላይ እንደሚቀመጥ ካሰበ በርካታዎቹ ዑለማዎች መፆም ግዴታ ይሆንበታል ብለዋል፡፡ [4]

21. ሀገሩ እያለ ፆምን ቢጀምር እና ከቀኑ መካከል ላይ ጉዞ ቢቀጥል ማፍጠር ይችላል ::

22. ምን ጊዜም ጉዞ ላይ ያለ የሚጠጋበት ሀገር ያለዉ ቢሆንም እንኳ ማፍጠር ይችላል (ለምሳሌ)፡-ፖስታ ቤት ሰራተኛ ፣ ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር ተመላላሽ ሾፌሮች ፣አዉሮፕላን አብራሪዎች እና አስተናጋጆች ጉዟቸዉ እለት በዕለት በየቀኑ ቢሆንም እንኳ (ነገር ግን) ቀዷ ማዉጣት አለባቸዉ፡፡ እንዲሁም የብስ ላይ መኖሪያ ያለዉ የመርከብ ሾፌር ::

---

[4] ይህ ገደብ ምንም ዓይነት መረጃ የለዉም ትክክለኛዉ እሚጓዝበት ሀገር እንደደረሰ እቀመጣለሁ የሚል ዉሳኔ ከወሰነ የመፆም ግዴታ አለበት ነገር ግን መቀመጥን ካልወሰን ማፍጠር ይችላል የሚለዉ አስተያየት ነዉ ::ተረጓሚው

23. ጉዞ ላይ የነበረ ከቀኑ መካከል ላይ አገሩ ቢገባ ጥንቃቄ ለማድረግ የወሩን ክብር ለመጠበቅ መከልከሉ ጥሩ ነዉ ነገር ግን ተከለከለም አልተከለከለም ቀዲ አለበት፡፡
24. ሀገር ላይ እያለ ፆምን ቢጀምር ከዚህ በኋላ ወደ ሌላ ሀገር ቢጓዝ እነዚህ ሰዎች ፆምን የጀመሩት ከነሱ በፊት ወይም በኋላ ቢሆንም ይህ ሰዉ የሀገሩን ህግ ሳይሆን የነዚህን ሰዎች ህግ መከተል አለበት፡፡

<u>የበሽተኛ ፆም</u>

25. ማንኛዉም በሽታ የሰዉ ልጅን ጤነኛ ከመባል እንዲወጣ የሚያደርገዉ ከሆነ ማፍጠር ይቻላል ፡፡ነገር ግን ቀላል ከሆነ (ለምሳል) ጉንፋን እና የራስ ምታት ይህን ምክንያት በማድረግ ማፍጠር አይፈቀድም፡፡
በሐኪም ቢረጋገጥ ወይም አንድ ሰዉ ከተሞክሮዉ፣ ከልምዱና ከጥርጣሬዉ አንፃር ፆም ቢፆም በሽታ እንደሚያመጣበት ወይም በሽታዉ እንደሚጨምርና እንደሚዘገይ ከተረዳ ማፍጠር ይችላል ይልቁንም መፆሙ ይጠላል፡፡
26. መፆሙ ለአዉድቅ በሽታ የሚዳርገዉ ከሆነ ያፍጥር እና ቀዲ ያዉጣ ከቀኑ መካከል ላይ አዉድቁ ቢጥለዉ ፀሀይ ከመግባቷ በፊት ወይም ከገባች በኋላ በሽታዉ ቢሻለዉ ፆሙ ትክክል ነዉ፡፡ ፆመኛ እስከሆነ ድረስ በሽታዉ የጀመረዉ ጎህ ከቀደደ (ከወጣ)ጀምሮ እስከ መግሪብ ድረስ ከሆነ በርካታዎቹ ዐሊሞች ፆሙ ተቀባይነት የለዉም ብለዋል፡፡ አዉድቅ በሽታ የጣለዉ የፈለገዉን ያህል ቢቆይበትም በርካታዎቹ ዐሊምች ቀዲ ማዉጣት ግዴታ ይሆንበታል ይላሉ፡፡
27. ገደብ ያለፈ ረሃብ ወይም ሀይለኛ የዉሃ ጥም ቢያደክመዉ በሕይወቱ ላይ ሞትን ከፈራ ወይም ከሰዉነቱ ክፍል ከፊሉ ከጥቅም ዉጭ ይሆናል የሚል ብዣታ ሳይሆን ጥርጣሬዉ ካመዘነ አፍጥሮ ቀዲ ያዉጣ ፡ ፡ ከባድ በሆነ ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ማፍጠር አይፈቀድላቸዉም ከቀኑ መካከል ላይ ስራዉን ቢያቆሙት ጉዳት የሚያመጣ እና በስራዉ ላይ ቢቀጥሉ በሕይወታቸዉ ላይ ሞትን የሚፈሩ ከሆነ ያፍጥሩ ቀዲ ያዉጡ፡፡
የተማሪዎች ፈተና በረመዷን እንዲያፈጥሩ የሚያደርግ በቂ ምክንያት አይደለም ፡፡
28. በሽተኛዉ በሽታየ ይወገድልኛል ብሎ ተስፋ ካደረገ እስከሚድን ድረስ ትግስት ያድርግ ከዚያም ቀዲ ያዉጣ ድሆችን ማብላቱ በቂ

አይደለም በሽተኛዉ በሽታየ ፈፅሞ አይወገድም የሚል እምነት ካለዉ እንዲሁም በዕድሜ የገፋ ሽማግሌ ሀገሩ ላይ ህዝቦች ከሚመገቡት በየቀኑ ላንዳንድ ድሃ የቁና ግማሽ ያብላ ::

29. ታሞ የዳነ ቀዲ ለማዉጣት ጊዜ እያገኘ ቀዲሳያወጣ ቢሞት ከንብረቱ ለያንዳንዱ ቀን ለድሃ የሚሰጥ መመደብ አለበት ከዘመዶቹ አንዱ ቢፆምለት ፆሙ ተቀባይነት አለዉ::

<u>የሽማግሌ የደካማና ያዛዉንት ፆም</u>

30. ሽማግሌ እና በዕድሜ መግፋት ምክንያት ጉልበቱ የደከመ አዛዉንት ፆም ግዴታ አይሆንባቸዉም:: መፆም የሚከብዳቸዉና የሚያንገላታቸዉ ከሆነ ማፍጠር ይችላሉ (ለየቀኑ አንዳንድ ድሃ ማብላት አለባቸዉ) ነገሮችን መለየት የማይችል እና ከቁጥጥር ዉጭ የሆነ አዛዉንት ግዴታ ስለሌለበት በሱም ላይ ሆነ በቤተሰቦቹ ምንም ነገር የለባቸዉም ::

3ነ. ከጥላት ጋር የሚፋለም ወይም ሀገሩ በጠላት የተከበበ መፆም ከመጋደል(ከመፋለም) የሚያደክመዉ ከሆነ ጉዞ ላይ እንኳ ባይሆንም ማፍጠር ይችላል:: እንዲሁም ከግድያ በፊት ማፍጠር ካስፈለገዉም ማፍጠር ይችላል::

32. ለማፍጠር ምክንያት የሆነዉ ነገር በግልፅ የሚታይ ከሆነ(ለምሳሌ):- በሽተኛ በግልፅ ማፍጠር ይችላል:: ግን ስዉር ከሆነ የወር አበባን ይመስል ሰዎች በመጥፎ ነገር እንዳይጠረጥሩት ተደብቆ ማፍጠሩ የተመረጠ ነዉ::

<u>ለመፆም ኒያ ማድረግ</u>

33. ፈርድ (ግዴታ) በሆነ ፆም ላይ ኒያ ማድረግ መስፈርት ነዉ:: እንዲሁም ዋጂብ(ግዴታ) የሆነን ፆም ቀዲበሚወጣ ጊዜ እና የከፍፋራ (ማበሻ) ፆም በሚጾም ወቅት ኒያ መስፈርት ነዉ:: ሌሊት በማንኛዉም ሰዓት ኒያ ማድረግ ጎህ ከመቅደዱ በፊት በተወሰኑ ደቂቃዎች ልዩነት እንኳ ቢሆን ኒያ ማድረግ ይቻላል::

ኒያ ማለት ለመፆም(ለመተግበር) እርግጠኛ በመሆን ሀሣብ ማሳደር ነዉ ባንደበት መናገር አዲስ ፈጠራ(ቢድዓ)ነዉ ረመዷንን የሚፆም ሌሊቶች በመጡ ቁጥር ኒያ ማደስ አያስፈልገዉም ይልቁንም ወሩ እንደገባ መጀመሪያ ላይ ኒያ ማድረጉ በቂ ነዉ::

34. ገደብ የሌለዉ ትርፍ ፆም ሌሊት ኒያ ማድረግ መስፈርት አይደለም:: ነገር ግን ገደብ የተደረገለት ትርፍ ፆም አህወጡ(ጥንቃቄ ለማድረግ) ሌሊት ኒያ ማድረግ በላጭ ነዉ::

35. ዋጂብ(ግዴታ) ፆምን ለመፆም የጀመረ (ለምሳሌ)፡-ቀዷ፣ ስለት እና ከፍፋራ(ማበሻ)መሙላት ግዴታ ይሆንበታል ::ያለ ምክንያት ማፍጠር አይቻልም:: ትርፍ ፆም ከሆነ ፆመኛዉ ራሱ ያዉቃል ከፈለገ ይፁም ከፈለገ ያፍጥር ምንም ምክንያት ባይኖረዉ እንኳ::
36. ረመዷን መግባቱን ጎህ ከቀደደ በኋላ እንጂ ያላወቀ ሰዉ ቀሪዉን ቀን መከልከል አለበት በርካታ ዐሊሞችም ቀዷ አለበት ብለዋል::
37. እስረኛ እና በሰዎች ቁጥጥር ስር የታገደ ራሱ ጨረቃን አይቶም ይሁን ታማኝ ሰዉ ነግሮት ወሩ መግባቱን ከተረዳ መፆም ግዴታ ይሆንበታል አልያም ትግል በማድረግ በግምት መጠቀም ይኖርበታል ::

<u>ማፍጠር እና መከልከል</u>

38. የፀሀይ ጨረር እንደገባ ፆመኛ ማፍጠር አለበት:: በአድማሱ ላይ የሚታየዉ ቀይ ነገር ግምት አይሰጠዉም ::
39. ጎህ ከወጣ ፆመኛ አዛን ይስማም አይስማም በፍጥነት መከልከል አለበት:: ለጥንቃቄ እየተባለ ጎህ ከመዉጣቱ በፊት የአሥር ደቂቃና ሌላም ደቂቃ ይሁን ልዩነት እያለ መከልከል አዲስ ፈጠራ (ቢድዓ)ነዉ::
40. በሃያ አራት ሰዓት ዉስጥ ሌሊትና ቀን የሚገኙበት ማንኛዉም ሀገር ቀኑ ረጂም ቢሆንም የመፆም ግዴታ አለባቸዉ::

<u>ፆምን የሚያበላሹ ነገሮች</u>

41. ከወር አበባና ከወሊድ ደም ሌላ ፆምን የሚያበላሹ ነገሮች የፆመኛዉ ፆም ለመበላሸት ሶስት መስፈርቶች መሟላት አለባቸዉ:: (ፆምን በሚያበላሸዉ ነገር) መሃይም ሳይሆን እዉቀት ያለዉ መሆን ፣ እረስቶ ሳይሆን እያስታወሰ እና ተቸግሮና ተገዶ ሳይሆን በምርጫዉ መሆን አለበት:: ፆምን ከሚያበላሹ ነገሮች(ለምሳሌ)፡-ግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም፣ አዉቆና ሆን ብሎ ማስታወክ ፣ የወር አበባ፣ መታገም[5]፣መመገብና መጠጣት ናቸዉ::
42. ምግብን እና ዉሃን የሚተኩ ነገሮች ፆምን ከሚያበላሹት ይመደባሉ:: ለምሳሌ፡- መድኃኒቶች እና በአፍ የሚዋጡ ክኒኖች ግን ምግብንና ዉሃን ሊተኩ የማይችሉ ለመድኃኒት ብቻ የሚገለገሏቸዉ ከሆኑ ፆም ላይ ችግር አያመጡም :: እንዲሁም የኩላሊት በሽታ ያለበት

---

[5] እዚህ ላይ ትክክለኛዉ ከመረጃ አንጻር መታገም አያስፈጥርም በመታገሙ ምክንያት ስለደከመ የሚያፈጥር ከሆነ መታገም ሀራም ይሆናል :: ግን ከመፆም የማያደክመዉ ከሆነ ይጠላል እንጂ አያስፈጥርም የሚለዉ ነዉ)::ተረጓሚው

ኩላሊቱን ቢያሳጥብ ፆሙ አይበላሽም ። በሰገራ መጠቀሚያ ላይ በመርፌ ምክንያት የሚገቡ መድኃኒቶች እንዲሁም የአይንና የጆሮ ጠብታ ፣ ጥርስ ማስወጣት እና ለቁስል መድሃኒቶች መጠቀም ፆም አያበላሽም። ለሳምባ ነቀርሳ በሽታ መድኃኒት ማስረጨትም ፣ ለምርመራ ደም መስጠት(መለገስ) አያበላሽም። ጣረ ሞት ላይ ለሆነ የሚሰጥ መድኃኒት እስካልዋጠዉ ድረስ አያበላሽም ለጥርሱ ማጠናከሪያ ያስጨመረ የዚህን ጣዕም ከጉሮሮዉ ላይ ቢያገኝ በፆሙ ላይ ችግር አያመጣም ።

43. ያለምንም ምክንያት በረመዷን ቀን አዉቆና ሆን ብሎ የበላ ወይም የጠጣ ትልቅ ወንጀል ፈፅሟል ተዉባህ ማድረግና ቀዷ ማዉጣት አለበት።

44. ፆመኛ መሆኑን ረስቶ የበላ ወይም የጠጣ ሰዉ ፆሙን ያሟላ ያበላዉና ያጠጣዉ አላህ ነዉና። ረስቶ የሚመገብን ፆመኛ ያየ ፆመኛ መሆኑን ያስታዉሰዉ።

45. የተከበረውን የሠዉ ልጅ ከሞት ለማዳን ማፍጠር ያስፈለገዉ ሰዉ ያፍጥር እና ቀዷ ያዉጣ ።

46. መፆም ግዴታ የሆነበት ሰው በረመዷን ቀን አዉቆና ሆን ብሎ በምርጫዉ ግብረ ስጋ ግንኙነት ቢፈፅም ፆሙ ይበላሻል።ተዉባህ ማድረግ ፣ ግንኙነት የተፈፀመበትን ቀን በፆም ማጠናቀቅ (በፆሙ ላይ መቀጠል) ፣ቀዷ እና ከፍፋራ(መቀጫ) ግዴታ አለበት። ይህ ህግ ዝሙትም ይሁን ግብረ ሰዶም እንዲሁም ድርጊቱ በእንስሳዎች ላይ ቢፈፀም ተመሳሳይ ነዉ።

47. ከባለቤቱ ጋር ግንኙነት ማድረግ ፈልጎ መጀመሪያ ምግብ በመብላት ፆሙን ቢያበላሽ ወንጀሉ በጣም የከበደ ይሆናል። በእርግጥ በመብላቱና ግንኙነት በመፈፀሙ የወሩን ክብር ሁለት ጊዜ ተዳፍሯል የመቀጫ የሆነዉ ከፍፋራም በጣም የከበደ ይሆናል።

48. ፆመኛዉ ነፍሱን መቆጣጠር የሚችል ከሆነ ከሚስቱና ከባሪያዉ ጋር መሳሳም ፣ መነካካት ፣ መተቃቀፍ፣መተሻሸት እና በተደጋጋሚ መመልከት ይችላል። ነገር ግን ስሜቱ ፈጣን ከመሆኑ አንፃር ነፍሱን መቆጣጠር የማይችል ከሆነ እነኝህን ነገሮች በሙሉ መራቅ አለበት።

49. ግንኙነት እያደረገ ጎህ ድንገት ቢወጣ በፍጥነት ግንኙነቱን ማቋረጥ ግዴታ ይሆንበታል ።ብልቱን ካወጣ በኋላ ፈሳሽ ቢወጣዉ

እንኳ ፆሙ ትክክል ነዉ አይበላሽም፡፡ ጎሁ እንደወጣ በግንኙነቱ ላይ ከቀጠለ ያፍጥር ተዉባህ ያድርግ ቀዷእና የመቀጫ ከፍፋራ አለበት፡፡
50. ጀናባ ሆኖ እያለ ቢነጋ ፆሙ ላይ ችግር አያመጣበትም፡፡ የጀናባ፣ የወር አበባን እና የወሊድ ደም ትጥበት ከፈጅር በኋላ ወዳለዉ ጊዜ ማዘግየት ይቻላል፡፡ ለሶላት ግን ግዴታ መታጠብ አለበት፡፡
51. ፆመኛዉ እንደተኛ በህልሙ የዘር ፈሳሽ ቢፈሰዉ ፆሙ እንደማይበላሽ ዐሊሞች ተስማምተዋል፡፡ በፆሙ መቀጠል አለበት፡፡
52. በረመዷን ቀን ሊጠነቀቀዉ በሚችለዉ ነገር ምክንያት (ለምሳሌ)፡- ብልትን በእጅ በመነካካት እና በተደጋጋሚ በማየት የዘር ፈሳሽ እንዲወጣዉ ያደረገ ወደ አላህ መመለስ እና ቀሪዉን ቀን መከልከል ግዴታ ይሆንበታል፡፡ ከዚያም ቀዷ ማዉጣት አለበት ::
53. ፆመኛ ሆኖ ሳይፈልግ ያስታወከ ሰዉ ቀዷ የለበትም አዉቆና ሆን ብሎ ያስታወከ ሰዉ ቀዷ ማዉጣት አለበት፡፡ ያስታወከዉ ከቁጥጥሩ ዉጭ ሆኖ እያለ ወደ ሆዱ ቢመለስ አያስፈጥረዉም :: የሚበጣጠስ ማስቲካ ወይም ጣፋጭ ነገር ማኘክ ሀራም ነዉ፡፡ ግን ወደ ጉሮሮዉ የሆነ ነገር ከገባ ያስፈጥረዋል :: አክታ እና ንፍጥ ወደ አፉ ከመድረሳቸዉ በፊት ቢዉጣቸዉ(ከጉሮሮዉ ላይ እያለ ቢመልሰዉ) ፆሙ አይበላሽም :: ግን አፉ ከደረሱ በኋላ ወደ ሆዱ ከመለሳቸዉ ፆሙ ይበላሻል፡፡ እንዲሁም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ምግብን መቅመስ ይጠላል፡፡
54. ፆመኛ በረመዷን ሙሉ ቀን ጥርሱን መፋቅ ሱና ነዉ፡፡
55. ማንኛዉም ፆመኛ በምርጫዉ ሳይሆን በድንገት ጉሮሮዉ ዉስጥ አንድ ነገር ቢገባበት (ለምሳሌ)፡-ነስር ፣ የቁስል ፈሳሽ ፣ዉሃ እና ቤንዚን ፆሙ አይበላሽም :: እንዲሁም የሚያለቅስ ሰው እንባዉ ጉሮሮዉ ዉስጥ ቢገባ ፣ ፀጉሩን ወይም ከላኛዉ ከንፈሩ ላይ የሚገኘዉን ፀጉር(ቀድሞ ቀመስ)ቅባት ቢቀባ እንዲሁም ሂናዕ ቢቀባና ጉሮሮዉ ዉስጥ ጣዕሙን ቢያገኝ አያስፈጥረዉም :: እንዲሁም ቁስል እንዲዘና እና ሰዉነትን ለማለስለስ የሚቀቡ ቅባቶች አያስፈጥሩም፡፡ ሽቶ ማሽተት እና የጭስ ሽታ ችግር የለዉም፡፡ ነገር ግን ጭሱ ጉሮሮዉ እንዳይገባ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ::
56. ጥንቃቄ ለማድረግ ሲባል ፆመኛ አለመታገሙ ይመረጣል (በዓሊሞች መካከል)ያለዉ ልዩነት ጠንካራ ስለሆነ፡፡

57. ማጨስ ፆም ያጠፋል(ያበላሻል)። ፆምን ለመተዉ ሱስ በቂ ምክንያትም አይደለም ።
58. ዉሃ ዉስጥ መዘፈቅ ወይም ሰዉነቱ እንዲቀዘቅዝ እርጥብ በሆነ ልብስ መጠቅለል ችግር የለዉም ።
59. ሌሊቱ ገና ነዉ በሚል እምነት ቢመገብ ፣ቢጠጣና ግንኙነት ቢፈፅም እናም ጎህ እንደቀደደ(እንደወጣ)ግልፅ ቢሆንለት ምንም አይነት ችግር የለበትም።
60. አንድ ሰው ፀሀይ ገብታለች በሚል ግምት አፈጠረ ነገር ግን ካፈጠረ በኋላ ፀሀይ አለመግባቷ ከተረጋገጠ ኡለማዎች ቀዷ አለበት ይላሉ)።[6]
61. አፉ ዉስጥ ምግብ ወይም መጠጥ እያለ ጎህ ቢወጣ ከአፉ ማዉጣት እንዳለበትና ፆሙ ተቀባይነት እንዳለዉ ዐሊሞች ተስማምተዉበታል።

<u>ሴቶችን የሚመለከቱ የፆም ህጎች</u>

62. ለአቅመ አዳም የደረሰች ሴት ሰዎችን ከመፍራቷ አንፃር ባትፆም ብታፈጥር ተዉባህ በማድረግ ቀዷ ከማዉጣት ጋር ሌላ ረመዷን እስከሚመጣ ድረስ ቀዷን ያዘገየች ከሆነ ለየቀኑ መቀጫ አንዳንድ ድሃ ማብላት አለባት ። እንዲሁም የወር አበባ በምታይበት ጊዜ ሰዎችን ከመፍራቷ አንፃር የፆመች ሴት ህግ ከዚህ ህግ ጋር ተመሳሳይነት አለዉ።
63. ሚስት ባለቤቷ እያለ በፍቃዱ ካልሆነ በስተቀር ከረመዷን ዉጭ ያለን ፆም መፆም አትችልም። ነገር ግን ከተሳፈረ ትችላለች።
64. የወር አበባ የምታይ ሴት ንፁህ መሆኗን የምታረጋግጥበት የሆነዉን ቀስሰተልበይዷዕ[7] ካየች ሌሊት ኒያ በማድረግ ትፁም። ንፁህ መሆኗን የምትለይበት ነገር ከሌላት በጥጥ ወይም በሌላ ነገር ብልቷን ትሸገዉ ያሸገችበት ነገር ንፁህ ሆኖ ከወጣ መፆም አለባት። የወር አበባ ወይም የወሊድ ደም የምታይ ሴት ሌሊት ደሟ ቢቋረጥና ለመፆም ኒያ ብታደርግ ከዚያም ከመታጠቧ በፊት ጎህ ቢወጣ ፆሟ ትክክል ለመሆኑ የሁሉም ዑለማዎች እምነት ነዉ።

---

6 እዚህ ላይ ትክክለኛዉ ንግግር ቀዷ የለበትም የሚለዉ ነዉ።ተርጓሚው

7 የወር አበባ ደም ሲቋረጥ ከመሀፀን የሚወጣ ነጭ ዉሃ ነዉ።

65. ከልምድ አንፃር ነገ የወር አበባ ይመጣብኛል ብላ የተረዳች ሴት ደም እስከምታይ ድረስ ማፍጠር አትችልም፡፡ በኒያዋ እና በፆሚ ላይ ትቀጥል፡፡

66. ሴት(ለፆም ብላ) የወር አበባዋን የሚያዘገይ መድኃኒት በመዉሰድ ከማቋረጥ ይልቅ አላህ የሰጣትን በደስታ በመቀበል በተፈጥሮዋ ላይ መቀጠሏ (መድኃኒት ሳትጠቀም) በደረጃ ይበልጣል ::

67. መፈጠር የጀመረን ፅንስ ያስወረደች ሴት ከወሊድ ደም ላይ ስለሆነች መፆም የለባትም፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የበሽታ ደም ስለሆነ የምትችል ከሆነች መፆም አለባት፡፡ የወሊድ ደም የምታይ ሴት ከአርባ ቀን በፊት ደሟ ከተቋረጠ መፆም እንዲሁም ለሶላት ገላዋን መታጠብ አለባት፡፡ ግን ደሟ ከአርባ ቀን የሚጨምር ከሆነ ለመፆም ኒያ ታድርግ እና ትፁም ገላዋንም ትታጠብ ከዚህ በኋላ ቀጣይ የሆነዉ ደም የበሽታ ደም ስለሆነ፡፡

68. የበሽታ ደም በፆም ላይ ችግር አያመጣም፡፡

69. የምትፈራ ነፍሰ ጡር እና እመጫት /የምታጠባ ሴት/ ከበሽተኛ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸዉ መሆኑ ተቀባይነት ያለዉ አቋም ማፍጠር ይችላሉ ከዚያም ቀዷ እንጂ ሌላ የለባቸዉም የሚለው ሀሳብ ነው፡፡ የሚፈሩት በራሳቸዉም ላይ ሆነ በልጆቻቸዉ ላይ የተሰጣቸዉ ህግ ተመሳሳይ ነዉ::[8]

70. መፆም ግዴታ የሆነባት ሴት በረመዷን ቀን ፍቃደኛ ሆና ባለቤቷ ቢገናኛት ኢስላም ለባለቤቷ ያስቀመጠዉ ህግ እርሷንም ይመለከታታል ነገር ግን ፍቃደኛ ሳትሆን ግንኙነት ላለመፈጸም ትግል እያደረገች አስገድዶ ከሆነ የተገናኛት ከፍፋራ (መቀጫ)የለባትም፡፡[9]

በመጨረሻም ከፆም ጋር ትስስርነት ያላቸዉ ጠቃሚ ነጥቦች አላህ እንዲወሱ ያገራቸው የሆኑት ይህን ይመስላሉ፡፡ ጌታችንን አላህን በብዛት እንድናወሳዉ እንዲሁም እንድናመሰግነዉና እርሱ በሚፈልገው ሁኔታ እንድናመልከዉም ያግዘን ዘንድ የረመዷንን ወርም የአላህን ምህረት

---

[8] ትክክለኛዉ ያፍጥሩ ለያንዳንዱ ቀን ድሃ ይመግቡ ቀዷማዉጣት <u>የለባቸዉም</u> የሚለዉ የኢብኑ አብባስ እና የኢብኑ ዑመር ንግግ የሆነዉ ይህ አቋም ነዉ፡፡

[9] ከፍፋራ (መቀጫ)ማለት አንድ ባሪያ ነፃ ማዉጣት ይህን ካላገኘ በተከታታይ ሁለት ወር መፆም ይህን ካልቻለ ስልሳ ድሃ ማብላት ነዉ፡፡

በማግኘትና ከእሳት ነፃ በመዉጣት የምንጨርስ እንዲያደርገን እለምነዋለሁ::እማጸነዋለሁ::
የአላህ እዝነትና ሠላም ለአገልጋዩ እና ለመልዕክተኛዉ ለሙሐመድ ﷺ እንዲሁም ለቤተሰቦቻቸዉ እና ለባልደረቦቻቸዉ ሁሉ ይሁን::

ትርጉም :- አቡዘር ሀሰን ኢማም

المترجم: أبوذر حسن إمام